የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ETHIOPIAN CHAMBER OF COMMERCE AND SECTORAL ASSOCIATIONS

ቀን 28-10-2008
Date

ቁጥር 02-420/106/1150
Ref. No.

ለትግራይ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለአፋር ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለሶማሌ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለሐረሪ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለድሬዳዋ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለአማራ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለደቡብ /ብ/ብ/ሕ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለጋምቤላ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለኦሮሚያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
ለኢትዮጵያ ስኳርና ጣፋጮች አምራቾች ማኅበር
ለኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር
ለኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማኅበር
ለኢትዮጵያ ሥጋ አምራች-ላኪዎች ማኅበር
ለኢትዮጵያ አበባ አትክልት እና ፍራፍሬ ላኪዎች ማኅበር
ለኢትዮጵያ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎች እና አዘጋጅቶ ላኪዎች ማኅበር
ባሉበት

**ጉዳዩ፡- የውጭ ኢንቨስትመንት ፎረም ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝን ይመለከታል፤**

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ‘‘Doing Business in Ethiopia: Opportunity for Foreign Investors’’ በሚል የአንድ ቀን ፎረም አዲስ አበባ ውስጥ በሐምሌ 21 ቀን 2008 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ጀምሮ በኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል ለማካሄድ አቅዷል፡፡

የፎረሙ ዓላማ በመላው ኢትዮጵያ ለውጭ ኢንቨስትመንት የተመቻቹ መልካም ዕድሎችን እና ምቹ የቢዝነስ ሁኔታዎችን ማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም የክልል የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የአባላት ተሳትፎ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ስለሆነም በፎረሙ ላይ የሚሳተፍ የክልሉ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አንድ ተወካይ እስከ ሐምሌ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ስሙንና የስራ ድርሻውን በኢ-ሜል፡ buyethiopian@gmail.com እንድትልኩልን እንጠይቃለን፡፡

ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባገኘነው መረጃ መሠረት ከክልል ለሚሳተፉ የአንድ ቀን አበል (መሄጃና መመለሻን ሳይጨምር) እና የትራንስፖርት (ለአውቶቡስ ብቻ ሆኖ በደረሰኝ የሚወራረድ) የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0911 30 35 85 አቶ ይምረሀ መኮንንን ማነጋገር ይቻላል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ቢንያም ምስጋና
የንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ
ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር

**ግልባጭ፡-**
- ለዋና ፀሐፊ ጽ/ቤት
- IT ክፍል

ኢ/ን/ዘ/ማ/ም/ቤት

Tel+251-11-5518240,5514005
Fax:+251-11-5517699
P.O.Box:517,Addis Ababa,Ethiopia
E-mail:etchamb@ethionet.et
WebSite:www.ethiopianchamber.com

የዓለም ዓቀፍ ንግድ ምክር ቤት አባል
Member of the International Chamber of Commerce